# አውደ ኢትዮጵያ

ግንቦት 25 2008 | የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት | እትም 7

## አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ / አንድነት/ መሥራች ጉባዔውን እንደሚያካሂድ ተገለጸ

አ/አ ግንቦት 22/2000 ዓ.ም.

በመጪው ሰኔ 7 / 2000 ዓ.ም.፤ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የመስራች ጉባዔውን እንደሚያደርግ ምንጮቻችን ከአዲስ አበባ አረጋገጡ። በተለይ ለ<u>አውደ</u> ዘጋቢዎች እንደተገለጸው ከሆነ፤ በዚሁ የመስራች ጉባዔ ላይ፤ 350 ያህል ጉባዔተኞች ከሀገሪቱ አራቱም ማዕዘናት ተሳታፊ ይሆናሉ። ከዚህ በተጨማሪም፤ 50 ታዛቢዎች በጉባኤው ላይ ይገኛሉ። በሃገር ውስጥ የሚገኙ፤ ምሁራን፤ የሀገር ሽማግሌዎችና ታወቂ ግለሰቦች፤ በታዛቢነት እንደሚገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም፤ ከሰሜን አሜሪካ፤ ከአውሮፓና ሌሎች አህጉራት ታዛቢዎች እንደሚሳተፉ ለማወቅ ተችሏል። ከጉበዔው አዘጋቾች በተገኘው መረጃ መሰረት፤ የጉባኤው ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ነው። ለጉባዔው የሚሆን ሰፊ አዳራሽ የተዘጋጀ ሲሆን፤ በዚሁ ጉባዔ ላይ ለመገኘት፤ ጉባዔተኞች በመጭው ሳምንታት፤ ወደ አዲስ አበባ እንደሚገቡ ለማወቅ ተችሏል። እንግዶቹን ለመቀበል የሚያስፈልጉ የመጨረሻ ዝግጅቶችም በመጠናቀቅ ላይ ናቸው። በዚሁ የመሥራች ጉባዔ ላይ፤ አንድነት ፓርቲ ያረቀቀው የፓርቲ ፕሮግራምና የመተዳደርያ ደንብ ላይ፤ ጥልቅ የሆነ ውይይት ይደረጋል። በዚሁ ረቂቅ ላይ፤ ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚገኙ፤ ደጋፊዎች፤ ባለሞያዎችና ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ ሰፊ ውይይተ በማካሄድ፤ እጅግ ገንቢ የሆኑ አስተያየቶች ሰጥተውባቸዋል። ጉባዔተኞቹ፤ እነዚህን ረቂቅ ሰነዶች፤ ያፀድቃቸዋል ተብሎ ይጠበቃል።

አንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ የሚለው ስምም ውይይት እንደሚደረግበት ለማወቅ ተችሏል። አንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ወይም በአጭሩ አንድነት የሚለው ስያሜ፤ ከእጅግ በራካታ ስሞች መሀከል ጥልቅ ውይይት ከተደረገበት በህዋል፤ የቀረበ ነው። ጉባዔተኛው፤ ስለስያሜው ማብራርያ በማዳመጥ፤ የበኩሉን ውይይት አድርጎ፤ ያጸድቀዋል ተብሎ ይጠበቃል። በዚሁ ጉባዔ ላይ፤ ከሚደረጉ አበይት ጉዳዮች ውስጥ፤ የአመራር አካላትን መመስረትና አባላቱንም ዲሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ መምረጥ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ጉባዔ፤ ብሔራዊ ምክር ቤቱንና ብሔራዊ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ይመሰርታል። ብሔራዊ ምክር ቤቱ 60 መደበኛና 15 ተጠባባቂ አባላት ሲኖሩት፤ እነሱም በዚሁ እለት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይመረጣሉ። ብሔራዊ የሥራ እሰፈጻሚ ምክር ቤቱ፤ ሊቀ መንበሩን፤ ሁለት ምክትል ሊቃነመናብርትንና ዋና ፀሃፊውን ጨምሮ፤ 13 አባላቶች ይኖሩታል። እነዚህ አባላት በዕለቱ በጉባዔተኛው የሚመረጡ ናቸው። ሌሎች የፓርቲው አካላትም በተዋረድ ይመሰረታሉ።

ጉባዔው፤ አንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ፓርቲን በመመስረት የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ተመራጭ አካላትም፤ አስፈላጊ የሆኑ ሰነድና መረጃዎችን በማጠናከር፤ ህጋዊ ዕውቅና ለማግኘት፤ ምርጫ ቦርድ እንደሚያመለክቱ ታውቋል።

<u>አውደ</u>፤ የጉባዔውን ሂደት ሙሉ ዝርዝር ዘገባ ይዛ እንደምትቀርብ፤ ለአንባብያን፤ ከወዲሁ ቃል ትገባለች።

## መብት የተሳትፎ ውጤት ነው

ከአባ ቀስቶ - ናሽቪል

ወያኔ-ኢህአዴግ ህገ-መንግስቱን ይፋ ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ ድርጊቶቹ ሁሉ ለይስሙላ በመሆናቸው ለውጭ ተመልካች እይታ አሳምሮ የሚቀባው ዲሞክራሲያዊ ቀለም ለጊዜው የምዕራባውያንን ህብስት ሲያወርድለት የኢትዮጵያን ህዝብ የዲሞክራሲ ተስፋ ግን አጨልሞበታል። ዛሬ የህዝቡ የፖለቲካ ንቃት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበትና አስመሳይነቱ ለዓለም በተጋለጠበት በዚህ ወቅት ወያኔ አፈና ከማድረግ ያለመቆጠቡ ለህዝቡ ምን ያህል ባእድ እንደሆነ በግልፅ የሚሳይ ነው። እነ መለስ ዜናዊ የህዝብን ፍላጎት እንዳላወቁና በአለም ፊት እንዳልተጋለጡ ሁሉ አይናችውን በጨው ታጥበው በክልልና በማሟያ ምርጫ አሸነፍን ሲሉ ተመጻድቀዋል።ወያኔ-ኢህአዴግ በዚህ ብቻውን ተወዳድሮ ባሸነፈበት ምርጫ ያሳየው ነገር ቢኖር ለህዝቡ ያለው ንቀት ብቻ ነው።

ለፓርላማው ድምቀት ሲሰጡ የቆዩት ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንኳን ባልተሳተፉበትና የወያኔ የአንድ ፓርቲ አመራር ተጠናክሮ ይፋ በወጣበት በዚህ ምርጫ ወቅት ተቃዋሚ ሃይሎች በድርጅቶቻቸው አማካይነት መቀራረብ፤ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ በግል የድጋፍ ተሳትፎን የበለጠ ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል ። ሊታገሉት የሚገባ የጋራ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ሃይል እያለ እንዲህ ተራርቀው የመኖራቸው ጉዳይ በእጅጉ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን እውነትም ለኢትዮጵያ ህዝብ በቁርጠኝነት መነሳታቸውን አጠያያቂ ያደርገዋል። ስለ ድርጅቶች ይህን ልበል እንጂ ኢትዮጵያዊያንም በግል የሚያሳዩት ተሳትፎ ወሳኝነት ያለው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። እኔም ማተኮር የምፈልገው በዚሁ ወገኖችሊያበረክቱት በሚገባቸው ጉዳይ ላይ ነው።

ሃገር እንዲህ ሲታመስና ታሪክ ሲቀለበስ እጅን አጣምሮ መቀመጥ እንዴት ያስችላል? ባሳለፍናቸው የትግል አመታት ለራስ ወዳድነትና ለአድር-ባይነት አስተዋጽዎ ያደረጉ አፍራሽ ክስተቶች ይኖራሉ ብዬ አገምታለሁ። "...የሞተልሽ ቀርቶ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## አንብበው ለወገን ያሰተላልፉ

# ኩማ ደመቅሳ፡ ያልተመረጡት ከንቲባ

## ርዕሰ አንቀጽ

የታሪክ ምሁራን እንደሚያስረዱት፤ አዲስ አበባ ከተማ የተመሰረተችው በአፄ ሚኒሊክ ነው። አፄ ሚኒሊክ እስከነጠራቸው እንጦጦ ተራራ ላይ ይሰፍራሉ። በዘመኑ፤ የጦር መሪዎች፤ ከጠላት ለመከላከል አመቺ የሆነ ስፍራ ፈልገው መስፈራቸው የተለመደ ነበር። እንጦጦ ደግሞ ከፍ ያለ ቦታ ላይ እንደመሆኑ መጠን፤ ጠራቸውን ለመከላከል ስለሚያመቻቸው፤ የአፄውን ቀልብ ለመሳብ ችሏል። በዚህን ጊዜ ነው፤ እቴጌ ጣይቱ፤ ወጣ ገባ በሚሉበት ጊዜ፤ ከእንጦጦ ግርጌ የሚገኘውን ስፍራ የቃኙት። በተለይም፤ ደግሞ ፍል ውሃውን ያዩና ይከጅሉታል። እሳቸው ከጅለው ታድያ፤ ማን ከልካይ አለ። አፄው ሳያወላዱ፤ ተራራ ወርደው አሁን አዲስ አበባ ተብሎ የሚጠራው ቦታ ላይ ሰፈሩ። ለሹሞቻቸውና ለባለሟሎቻቸውም ቦታ ሸንሽነው ሰጡ፤ እንዲህ እንዲ እያለ ከተማ እየመሰለ መጣ። አዳዲስ ነገር እንደሚወዱ የሚነገርላቸው አፄ ሚኒሊክ፤ ቴክኖሎጂን ወደሀገር በማስገባት ረገድ ቀደምትነት ያላቸው አፄ ሚኒሊክ፤ ዉሃን በቤተመንግስት አስገቡና እብዲህ ተብሎ ተገጠመ፦

ምንያለ ንጉስ ነው
    እንዲህ የተቀናጣ፤
ዉሃ በመዘውር
    ከእልፍኙ ያስመጣ።

እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፤ እስከ ምርጫ 97 ድረስ፤ ከተማዋ ብዙ አስተዳዳሪዎችን/ ከንቲባዎችን አስተናግዳለች። ከመቶ ዓመት በላይ እድሜ ያላት ከተማችን፤ ብዙ የተጓዘች ብትሆንም፤ በሃገሪቱ ከሚገኙ ሌሎች ከተሞች የተሻለች መስላ ብትታይም፤ ማደግ ከነበረባት አንጻርና ከሌሎች በአፍሪቃ ከሚገኙ ‘አቻ’ ዋና ከተማዎች ጋር ስትወዳደር፤ የአፍሪቃ አህጉር መነኻርያ ከመሆኗ አንፃር፤ እጅግ ብዙ ይቀራታል። በአሁኑ ወቅት የህዝቧ ብዛት በአስደንጋጭ ሁኔታ ከ4-5 ሚሊዮን ይደርሳል። የእህል ዉሃ ነገር ሆኖ፤ በየዕለቱ ከሀገሪቱ አራቱም ማዕዘን በብዛት ህዝብ ይጎርፉል። የተፈጥሮ ህግ ሆኖ ደግሞ፤ አዲስ አበቤው ዕለት በዕለት የራሱን ቁጥር ይጨምራል። ችግሩ፤ ከተማው ይህን ሁሉ ህዝብ ለማስተናገድ ዝግጁ አይደለችም። መብራት በራሽን ነው፤ ጭርሱንም የማይደርሰው ህዝብ ቁጥር ቀላል አይደለም። ውሃ በሳንቲም እየገዙ፤ በባልዲ እየቀዱ መጠቀም፤ አዲስ አበባ እምብርት ላይ የሚያስገርም አይደለም። እጅግ አብዛኛው ህዘብ መፀዳጃ ቤት የለውም። የከተማዋም አብዛኛው አከባቢ ንፁህ አይደለም። የፅደት አገልግሎትም የሚሰጠው በጣም ውስን ነው። ከተማው መንገድ የለውም፤ ያሉትም ቢሆኑ የፈራረሱ ናቸው፤ የእድሳት ጊዜያቸው ካለፈ ዓመታት ተቆጥረዋል። በርከት ያሉ አዳዲስ ሰማይ ተቀስ ህንፃዎች የተገነቡ ቢሆኑም፤ ውስጣቸው ባዶ ነው። አቅም ኖሮት፤ ገዝቶም ሆነ ተከራይቶ ህንፃዎቹን ጥቅም ላይ ለማዋል የቻለ የለም። ከተወሰኑ ፎቆች በላይ ደግሞ ዉሃ አቅም ኖሮት ሽቅብ መውጣት አልቻለም።

ከህንፃዎቹ ሥር፤ ህንፃዎቹን ውበት፤ በሚያጋልጥ መልኩ፤ ቤት የሌላቸው፤ ላስቲክ ከልለው ኮልኩለው ይኖራሉ። ምፀት። የእንደኒዚህ ዓይነቱን ነዋሪዎች ብዛት ለማወቅ ባይቻልም ግን፤ በየህንፃው ስር፤ በየቤተክርስትያኑ ሥር፤ በየአውቶቡስ ጣብያው ሥር፤ በየወንዙና ድልድዩ ሥር፤ የቀኑን ፀሃይ የሌቱን ብርድ ችለው፤ የፈጣሪ ፈቃዱ ከሆነ ቆርሰው፤ የሚቆርሱትን ያጡም እንደሆነ ተመስገን ብለው ስም ኖሯቸው ስም እንደሌላቸው አህዝ ብቻ ሁነው፤ በብዙ ሺህ የሚቆተሩ ተብለው ይኖራሉ። እንደየሰዉ ሁሉ፤ ከእንቅልፋቸው ይነሳሉ፤ ሸለብም ያደርጋቸዋል፤ እስከወድያኛው እስከሚያሸልባቸው ድረስ።

ኢህአዴግ ቦዘኔ ያላቸው እነሱ ግን ሥራ አጥ የሆኑ ደግሞ፤ እንደዚሁ በራካታ ናቸው። ጉልበት አላቸው፤ ዕውቀት አላቸው፤ እንደየደረጃቸው ከተለያዩ ተቋማት ተመርቀዋል፤ ችሎታ አላቸው ሆኖም ግን ሥራ የላቸውም። የመንገስት ስራ የለም፤ ጭርሱኑ ሥራ ያላቸውም እየተባረሩ ነው። የግል ሥራ የለም፤ ከጥቂቶች በስተቀር ሀብት፤ ጉልበት፤ ዕውቀት አፍስሰው ልማት ማካሄድ አልቻሉም። ቢሮክራሲው፤ ምዝበራው፤ በዘመድ አዝማድ፤ በዘር ሀረግ መጠቃቀሙ፤ ልሥራ ባዩን አሽሽቶታል። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ ሥራ እንዳይሰሩና እንዳያሰሩ፤ ደግሞ በቅርቡ፤ ኢህአዴግ አስገራሚ ፡የሆነ / ከእንግዲህ በኢህአዴግ መገረም መተው አለብን/ ፤ ህግ አወጣ። በስራ ገበታቹህና በየስብሰባዎቻቹህ ሁሉ አንድ አንድ የመንግስት ተወካይ /ሰላይ/ መገኘት አለበት የሚል።

በአንድ ወቅት ኢህአዴግ የአዲስ አበባን ችግር ለመቅርፍ ጥናት አደረኩኝ አለና፤ የጥናቱን ውጤት አስቋጥሮ፤ አቶ አርከበ እቁባይን ሾመ። እሳቸውም ካብኔያቸውን ሰየሙ / የተሰየመላቸውን ወሰዱ/። ችግር ደህና ሰንብች ለአዲስ አበባ ህዝብ መግለጫ ተሰጠ። ብዙም አልቆየ፤ በንጉሱ ጊዜ የተሰሩ፤ በደረግ ጊዜ የተወረሱ፤ ቤቶች፤ በኢህአዴግ/ወያኔ/አርከበ ጊዜ መፍረስ ጀመሩ። ሱቅ በደረቴ ነጋዴው ተባረረ፤ ሌላው ቀረጥ ካቅም በላይ ተጥሎበት ንግዱን ትቶ ወዴት እንደሄደም አልታወቀም፡፤ ከተማዋን እናፀዳለን አሉ፤ የጋሽ አበራ ሞላን የፀዳት ፕሮጀክት አስቆሙ። ‘የልማት’ ጉዞው ቀጠለ ሥራ አጡ በረከተ፤ መንገድ አዳሪው፤ጾም አዳሪው እንደ አሸን ፈላ። በመጨረሻም፤ ሹመኛው አቶ አርከበ ዕቁባይ፤ በቁንጮው ሰውዬ፤ ‘ብዙ ድስት ጥዳ ወጢ ያረረባት’ ተብለው ተወረፉ፤ መልስ አይሰጡ ነገር.... .

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ምርጫ ምርጫ ያውም ነጻ ምርጫ ተባለ። ህዝቡ አላምን አለ። ኢህአዴግ ማለ ተገዘተ። ተቃዋሚዎች እስኪ እንሞክረው አሉ፤ በምርጫም ተወዳደሩ። ኢህአዴግ ቀረጥ እሰርዛለሀኝ ቢል፤ አቶ አርከበ ባለታክሲዎችን ሰብስበው ቅጣታቹህ ተሰርዟል ብቻ የምርጫው ዕለት አደራ ቢሉ፤ ኢህአዴግ ብርና ከኔተራ ሰጥቶ ህዝቡን ሰልፍ በግድ ቢያስወጣም፤ የአዲስ አባበ ህዝብ ግን በሳምንቱ እጥፍ በእጥፍ፤ ሁኖ የሱናሚ ሰልፍ ወጣ፤ የልቡን በልቡም ይዞ፤ ግንቦት 7 ዕለት ቅንጅትን መረጠ። በተለይ በአዲስ አበባ የተካሄደው ምርጫ፤ በነጭ ታዛቢዎች ሥር በመሆኑ፤ ኢህአዴግ እጅ ለመስጠት ተገደደ። _ከተማዋም ለመጀመርያ ጊዜ ተመራጭ ከንቲባዋን አገኘች።_ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ራዕይ ሰንቀው፤ ዕውቀት ሀብት ጉልበት ያላቸውን አሰባስበው፤ አዲስ አበባን አዲስ ለመድረግ፤ የኢትዮጵያና የአፍሪቃ መዲናነቷን ክብር የሚመጥን ዕድገት ለማምጣት፤ ቆረጡ። ኢህአዴግም ይህንን በመፍራት፤ በየጀምበሩ አዳዲስ ህግ በማውጣት፤ የዶ/ር ብርሃኑ ሥራ ከጅምሩ ከባድ ለማድረግ ውጤቱንም ከወዲሁ ባዶ ለማድረግ፤ የጉልበትና የማን አለብኝነቱን ተያያዘው። በዚህ መሓል፤ ቅንጅት ፓርላማም ሳይገባ ቀረ፤ አዲስ አበባንም ሳይረከብ ቀረ። በከተማዋ ታሪክ የመጀመርያው ተመራጭ ከንቲባ፤ መመረጣቸው ወንጀል ሆኖ፤ ወህኒ/ ቃሊቲ ወረዱ፤ ‘ይቅርታ’ ጠይቀው ተለቀቁ፤ ከዚያም ወደስደት።

አቶ አየለ ጫሚሶ፤ ጓደኞቻቸው መታሰራቸውን ሲያዩ፤ የዕለቱን ብቻ በማየት፤ ጊዜ የማይደርስ መስሏቸው፤ ቅንጅት እኔ ነኝ ፤ አዲስ አባበንም እረከባለሁ፤ ከንቲባም እሆናለሁ አሉ። ኢህአዴግ ቼ ፈረሴ አላቸው፤ አንድ አንድ አምባሳደሮች፤ ገንዘብም እንሰጣለን እስከማለት ደረሱ። ዛሬ ሁለት ሰው ጎደለ፤ ነገ ሶስት ሰው ጎደለ ሲባል፤ ሰው ማሟላት አቅቷቸው፤ አዲስ አበባን መረከብ አቃታቸው፤ ከንቲባም ሳይሆኑ ቀሩ።

አቶ መለስ ይህን ጊዜ፤ አወጡ አወረዱና፤ ልክ በአቶ አርከበ እንዳደረጉት ሁሉ፤ ጊዜያዊ /Care Taker / የሞግዚት አስተዳደር ለአዲስ አበባ ህዝብ ሰጡት። አቶ ብረሀኑ ደሬሳም ከንቲባ ተብለው ተሾሙ፤ ሳይመረጡ። ለስድስት ወር ተብለው የተሾሙት የአዲስ አበባ ሞግዚት

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ኩማ ደመቅሳ...

ከገጽ 2 የዞረ

ከንቲባ፤ ከሁለት አመት በላይ ቆዩ። በመሀሉም፤ "እንኳን አዲስ አበባን የኔን የቢሮ ሽንት ቤት እንኳን ማጽዳት አልቻልንም" አሉ። ካብኔያቸውንም አንዴ ሲያፈርሱ፤ አንዴ ሲያዋቅሩ፤ የአዲስ አበባ ህዝብ ግን ያው በገሌ እንዳለ ከረመ።

አይደርስ የለም፤ የአዲስ አበባ ህዝብ እንደ ፈጣሪው ቸርነት፤ ለሁለተኛው ምርጫ ደረሰ። ቅንጅት የአዲስ አበባን ምክርቤት ስላልተረከበ፤ የማሟያ ምርጫ ይደረጋል ተባለ። በዚህኛው ዙር ምርጫ፤ ኢህአዴግ አውቆበታል። የህዝብ ድጋፍ እንደሌለው ፍፁም
እርግጠኛ ነው፡፤ ስለዚህ ምርጫውን ነጻ ማድረግ የማያዋጣ ነው። ታዛቢ የሚባል ነገር ከለከለ፤ ተወዳዳሪ ሚባል ነገር አባረረ፤ አራት ሚሊዬን ዕጩ ተወዳዳሪ አቀረብኩኝ አለ፤ 26 ሚሊዮን ህዝብ መረጠ አለ፤ ( አንድ ተወዳዳሪ ቢበዛ 8 ሰው ነው የመረጠው ማለት ነው)። በመጨረሻም፤ ውጤቱስ ሲባል፤ ከአንዲት በሕይወት የሌሉ ግለሰብ በስተቀር በአዲስ አበባ 'ሙሉ በሙሉ ተመረጥኩኝ' አለ። ህዝብም ዝም አለ፡፤ የዝምታ ተቃውሞ። አዲሶቹ 'ተመራጮች' ተሰባሰቡና አቶ ኩማ ደመቅሳን 'የመጀመርያው ተመራጭ ከንቲባ' ብለው ሾሟቸው፡፤
አቶ ኩማ ደመቅሳ፤ ለሹመት አዲስ አይደሉም። የደርግ ወታደር ሆነው በወያኔ የትግል ሜዳ ላይ ተማረኩ። የወያኔን 'ተሃድሶ' ኮርስ ወስደው እጅግ አጥጋቢ ውጤት በማስመዝገባቸው፤ ከመሰሎቻቸው ጋር በመሆን በወያኔ ፍፁም ቁጥጥር ስር የሚገኘውን፤ ኦህዴድን አቋቋሙ። ሊቀመንበርም ሆኑ። ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠርና መንግስት ሲሆን፤ እሳቸው የመከላከያ ሚኒስትር በመሆንም ተሹመዋል። የኦሮምያ ክልል ፕሬዝዳንትም ተብለዋል። የህዋላ ህዋል፤ ከአንድ አንድ ጓዶቻቸው ጋር በመሆን፤ የወያኔውን ቁንጮ ወንበር ለማስለቀቅ ሲሞክሩ በድጋሚ ተማረኩ። በድጋሚ ተሃድሶ ገብተው፤ ምህረት ለምነው፤ ምህረት አገኙ። የዚህ ሀላፊ፤ የዚያ ሚኒስተር ሲሉ ከራረሙና፤ ይኸው የወያኔ/ኢህአዴግ ሁለት ጊዜ ምርኮኛ የሆኑት አቶ ኩማ ደመቅሳ የአዲስ አበባ ከተማ 'ተመራጭ' ከንቲባ ተባሉ።

የተመረጡት ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ቢሆንም፤ በነዚህ ሁለት ዓመታት ውስጥ አደስ አባባን በዕድገት ጎዳና ይዘዋት እንደሚገሰግሱ ፎከሩ። ተሰናባቹ፤ የሞግዚት ከንቲባ በርክክቡ ወቅት ስለስራቸው ሲናገሩ 'ከምርጫ 97 ግርግር በህዋላ፤ ህዝቡን በማረጋጋት ወደ ሥራ እንዲሰማራ ማድረጋችን ትልቅ ድል ነው' ነበር ያሉት።

በሁለት ዓመት ውስጥ የሞግዚቱ አስተዳደር መስራት የቻለው ትልቅ ሥራ ይህ ከሆነ፤ በመጪው ሁለት ዓመታት አዲሱ ተሿሚ ከንቲባ ምን ይሰሩላት ይሆን? ጊዜ ያሳየናል።

አሁን ዛሬ ላይ ቆመን የምናውቀው ነገር ግን ከንቲባ ኩማ ደሜቅሳ በህዝብ የተመረጡ አይደሉም።

## የመሪ ያለህ

**ከፕሮፌሰር አዱኛው ወርቁ**

የኢትዮጵያ አምላክ የድሮው የጥንቱ
በመከራዋ ቀን የደረስክላቱ
ዛሬም እንደገና እጇን ስትዘረጋ
ከሚያንዣብብባት ውስብስብ አደጋ
መለስ አርገህ አውጣት በምታውቀው ዘዴ
ከሥራት ካፈና ከጦር ከጎራዴ።
አንተን ተስፋ አድርጋ፤ አንተኑ ተማምና
በመቅደስ በመስጊድ ዉት ማታ ለምና
ወደአንተ ስትመጣ እርዳታ ፈልጋ
ያዛት እንደድሮው እጇን ስትዘረጋ።
እባክህ አምላክ እባክህ ፈጣሪ
በሥርዓት በፍትህ ህዝብ አስተዳዳሪ
የወገኑን ችግር ተካፋይ ተጋሪ
ስጣት ለኢትዮጵያ ዕውነተኛ መሪ።
ውሃ ቀጥኗል ብሎ ቶሎ የማያኮርፍ
አይቶ የሚታገስ ሰምቶ የሚያሳልፍ
ለወገን የሚያስብ ልበ-ሰፊ መሪ
ስጣት ለኢትዮጵያ እባክህ ፈጣሪ።
ጉልቻ ቢቀየር ወጥ አያጣፍጥምና
ከዘንድሮው ስህተት ካምናው ከታቻምና
ትምህርት የተማሪ መሪ ስጠውና
ሕዝቡ ይገላገል ከሥራት ካፈና።
ትንንሹ ነገር እየተጋነነ
እንደተለመደው እንዳምነው ከሆነ
ወይም እንዳለፈው ወይም ካለፈው ብሶ
በሽታው ከመጣ መልሶ መላልሶ
ምን እንሸር ብለን ነው የምንጠጣው ኮሶ?
ዲሞክራሲ ፍትህ በሀገሩ እንዲስፋፋ
ሕዝብ እንዲተባበር በፍቅር በተስፋ
ተከታይ አይደለም መሪ ነው የጠፋ።
እሱ ያወታውን ህግ የማያከብር
ተባብሮ የማይሰራ በአንድ ድርጅት ሥር
እንዴት አድርጎ ነው ሕዝብ የሚያስተዳድር?
እኔ ያልኩት ይሁን ሌላው ገደል ይግባ
በማለት ለመጥለፍ አንዱ አንዱን ሲያደባ
ማየትና መስማት ያሳዝናል በጣም
አገር የሚያስቀድም እንዴት መሪ አይመጣም?
ለወገን የሚያስብ እንዴት መሪ አይመታም?

የመሪ ያለህ።
ለፍትህ ለእውነት ለነፃነት ብሎ
የቅንጅትን ቃል ጥሪ ተከትሎ
ያ ሁሉ ሰው ሞቶ ያ ሁሉ ሰው ቆስሎ
ያ ሁሉ ሰው ታስሮ ስንቱ ተፈናቅሎ
ያ ሁሉ መስዋዕት አይከፍሉ ተከፍሎ
ባለመደማመጥ ባለመከባበር
ባለመስተዋወል ባለመተባበር
በየምክንያቱ ሲጯጯህ ሲናቆር
የወገናችን ደም እንዴት መና ይቅር?
እንዲህ ሊዘረገፍ ተቋጥሮ ሊፈታ
መሪ አገኘሁ ብሎ ህዝቡ እየተመካ
ደሙን ያፈሰሰው በከንቱ ነው ለካ።
መቻቻል ሳይማር አንዱ ከአንዱ ጋራ
በአግባቡ ሳይወጣ የህዝቡን አደራ
ራሱ ባወጣው በህጉ ሳይሰራ
ደንቡን ተከትሎ ድርጅት ሳይመራ
ዲሞክራሲ! እያለ ሺህ ጊዜ ቢያወራ
አቤት የሚል የለም እንዲህ በቀላሉ
ድስኩርና ምግባር ሳይመሳሰሉ።
ልብ ስጠን እንደ አለት ጠንካራ
ለሀገር ለወገን አብረን እንድንሰራ።

የመሪ ያለህ!
በፍርሃት በጭንቀት ሁሌ መባነኑ
መታሰር፤መገረፍ፤መሞት ነታፈኑ
ወገኑን ወገኑ እንደ አውሬ ማደኑ
ሰልችቶናልና መሰደድ ማዘኑ
እኛንም ለውጠን ልክ እንደዘመኑ።
በሀሳብ በተግባር መለያየታችን
ጠላት ካደረገን እርስ-በርሳችን
በሰላም ካልፈታን አምቧጓሮ ችግር
ዲሞክራሲ ፍትህ እያልን መዶናቆር
ምን ትርጉም ይሰጣል እስቲ እንነጋገር።
እንዴት አንማርም ከታሪክ ካለፈው
ተባበሩ እያለ ከሚለፈልፈው።
የመሪ ያለህ!
በተፈጥሮ በድርቅ እየተመካኘ
በአየሩ በአፈሩ እየተመካኘ
የኢትዮጵያ ችግር ሰው ሁኖ ተገኘ።
ያውም የማይማር ከታሪክ ካለፈው
ተባበሩ እያለ ከሚለፈልፈው።
ከጥፋት ላይ ጥፋት ከበደል ላይ በደል
ለማንም የማይበጅ ተያይዞ ገደል
መሆኑን ተረድተን እንድንተባበር
በዚህ አዲስ ዘመን በዚህ አዲስ ጅምር
አዲስ መንፈስ ስጠን እባክህ እግዚአብሔር።
እንዳልናገረው ጉዱ የኔ ሁኖ
ከሆዴ ያለው ጭስ ገደለኝ አፍኖ።
የተባለው ነገር በኢትዮጵያ ህዝብ ደርሶ
እንደውሽማ ሞት ውስጥ ውስጡን አልቅሶ
የመሪ ያለህ! ይላል፤ መልሶ መላልሶ
በቃን መገዳደል በቃን ጠርነት
በቃን መጣላለፍ በቃን እስራት

# ገበሬው ነፃ ካልሆነ ችጋር ሁልጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራል

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

ችጋር ሁላችንም አልፎ አልፎ የምናውቀው ረሃብ አይነት አይደለም። ችጋር በአንድ አከባቢ ብቻ የሚኖሩ ሰዎችን በአንድ ጊዜ የሚያጠቃ የህብረተሰብ በሽታ ነው። ችጋር ምንም የሚላስ የሚቀመስ በመጥፋቱ ሰዎች በአካላቸው ውስጥ በአከማቹት እየተጠቀሙ፤ ዕለት በዕለት አካላቸውን እየጨረሱ፤ እያወቁት ቀስ በቀስ ወደተረጋገጠ ሞት የሚሄዱበት የህብረተሰብ በሽታ ነው። ቤተሰብ ይፈርሳል፤ ህብረተሰብ ይፈርሳል። ባል ለሚስቱ፤ እናት ለልጇ፤ ዘመድ ለዘመድ ያለው ፍቅርና ቅን መንፈስ ሁሉ ተንኮታኩቶ እያንዳንዱ ሰው ለብቻው የየራሱን ጻዕር እያብሰለሰለና እያቃሰተ የሚደቆስበት በሽታ ነው። ሕፃን ልጅ የእናቱ ጡት መድረቁን ባለማወቁ እያኘከ የቦጨቃቸውን ጡቶች አይቻለሁ፤ እናቲቱም በባሰ የችጋር ሕመም ተይዛ ከእንዲህ አይነቱ ሕመም ውጭ ነበረች።

ችጋር የሰው ልጅ እንደማገዶ እንጨት ተለብልቦ የሚያልቅበትና ቀባሪ እንኳን የማያገኝበት የውርደት ሞት ነው። የሰው ልጅ ውርደት ነው፤ የሕብረተሰብ ውርደት ነው፤ የሀገር ውርደት ነው። ቁራሽ እንጀራ ወይም እፍኝ ቆሎ የሚሰጥ ዘመድ ወይም ወዳጅ ወይም ወገን ጠፍቶ፤ ለነፍሱም ይሁን ለሰብአዊ ርህራሄ ተነሳስቶ፤ የሚረዳ ጠፍቶ በሺህና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየቤታቸው፤ በየመንገዱና በየገበያው የሚወድቁበት ሁኔታ ነው።

ችጋር የሚመጣው በድርቅ ወይም በተምችና ሌሎች የሰብል ተባዮች ወይም በዝናምና ብዛትና በበረዶ ወይም እግዚአብሔር በመቆጣቱ ወይም በእነዚህ ሁሉ ነው ይባላል። እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሚደረደሩት ሆን ተብሎ በማንም ላይ ሃላፊነት እንዳያርፍ ለማድረግ ነው። ሁሉም ከእውነት የራቀ ነው። እውነቱ ነገር እነዚህ ሁሉ የተፈጥሮ ችግሮች በብዙ አገሮች ይከሰታሉ፤ ሆኖም በዚህ ምክንያት ሰዎች በችጋር አለማለቃቸው ነው። እውነቱ ነገር ችጋር የአገዛዝ ሥርዓት ውጤት መሆኑ ነው። እውነቱ ነገር ችጋር ህብረተሰቡ በአገዛዝ ሥርዓት ደንዝዞና በራሱ የኑሮ ትግል ተተብትቦ የመተሳሰብና የመረዳዳት መንፈሱ የተሟጠጠ መሆኑ ነው። እውነቱ ነገር ችጋር የሚጀምረው የድርቅ ወቅተ ከመድረሱ በጣም ቀድሞ መሆኑ ነው።

ለብዙ ሰዎች ግራ የሚያጋባው ነገር በችጋር የሚጠቁት ገበሬዎች በተለይም የምግብ እህልን የሚያቀርቡት መሆናቸው ነው። ለምሳሌ የቡና ገበሬዎች በችጋር እምብዛም አይጠቁም። ይህ የሚሆንበት ራሱን የቻለ በቂ ምክንያት አለ።

1ኛ እህል የሚያመርቱ ገበሬዎች አብዛኛውን ጊዜ ለራሳቸው የሚሆን ምርት ያመርታሉ እንጂ በገበያ የበለጠ ዋጋ ያስገኝልናል በማለትና ከገበያም በርካሽ ዋጋ ሌላ እህል ለራሳችን እንገዛለን ብለው ሂሳብ አስልተው አይደለም።

2ኛ በብዙ ምክንያቶች ምርታችው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸውም ከአዝመራ እስከ አዝመራ የሚያደርሳቸው አይደለም።

3ኛ አዝመራቸውን ጠብቀው የሚመጡና ምርታቸውን የሚሻሟቸው ቀበኞች ብዙ ናቸው። ግብር አስከፋዩ፤ በልማት ስም የማያልቁና ማቋረጫ የሌላቸው የመብዝበዥያ መዋጮዎችና ለገበሬው በአራጣ ያበደሩ ሁሉ ገበሬውን የአዝመራውን ጊዜ ጠብቀው ያራቁጡታል። ገና በልቶ ሳይጠግብ ወጥረው ለሚይዙት ለእነዚህ ቀበኞች መክፈል አለበት፤ ያለበለዝያ መታሰርና መጉላላት የማይቀር ነው። አሁን ደግሞ የማዳበርያ ዕዳ ተጨምሯል። በአዝመራው ጊዜ ገበሬው ስለሚወጠር፤ እህሉን መሸጥ ይኖርበታል።ገበሬው ሁሉ እህሉን በአንድ ጊዜ ወደገበያ ያወጣል፤ ዋጋው አሽቆልቁሎ ይጠብቀዋል። ግደተታውን ለመወጣት በርከት አድርጎ ለመሸጥ ይገደዳል። ከገበሬው የመኖር ግዴታ የቀበኞቹ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ይበልጣል፤ ይቀድማል።

ችጋርን ጸንሶ የሚወልደው የአገዘዝ ሥርዓት ግፍ ነው። ይህንን ዕውነት ሳይረዱ ችጋርን እናጠፋለን የሚሉ፤ ችግሩን አልተገነዘቡትም ወይም ሊገነዘቡት አልፈለጉም። ችጋርን ማስወገድ የሚችሉት ገበሬዎች ብቻ ናቸው፤ የራሳቸው ባለቤቶች ለመሆን ነፃነታቸውን ሲያገኙ።

ችጋር እንደ ደራሽ ውሃ ወይም እንደ እሳት ቃጠሎ ወይም እንደ መሬት መንቀጥቀጥ በድንገትና ሳይታሰብ የሚመጣ አደጋ አይደለም። ችጋር ሰዎችን ወደአስከፊ የጅምላ ሞት ለሚያደርስ ቢያንስ ሰባት ወር ይፈጃል። የገበሬው ኑሮ በተለይ የምግብ ፍጆታው ማሽቆልቆል የሚጀምረው ገና የአዝመራው ወራቱ ሳያልቅ ነው። ይህ የምግብ ፍጆታው ማሽቆልቆል የሚጀምርበት ጊዜ ክረምት ከመግባቱ በጣም ቀድሞና የድርቅ ጉዳይ ገና ሳይሰማ ነው።

<u>ችጋርና ልመና</u>

ከደርግ ጊዜ ጀምሮ በ76ቱና በ77ቱ ችጋር ብዙ የዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ገቡ። እነዚህ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች እህል እያመጡ ለገበሬው በያለበት ያድላሉ፤ ምግብ ለሥራ እንደዚህ እያሉ ከ77 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እንደቀጠለ ነው። እነዚህ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ችጋር ሥራቸው አድርገው ዋናውን ሥራቸውን እዚሁ ተከሉ። እንደውም ትንሽ የዝናብ እጥረት ያለ እንደሆነ እሪ ይላሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ቶሎ ይወጣል። ስለዚህ ወደሞት ደረጃ ሳይደረስ እህል እያመጡ ያከፋፍላሉ። ሌላው በደርግ ጊዜና በወያኔ ዘመን የተለመደ ነገር ምንድን ነው፤ አንዳንዶቹ የዚህ ሃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች አሉ። የመንግስት ለማኞች። አንድ የእርዳታ አስተባባሪ ድርጅት ወይም ሌላ ስም ይሰጠው የልመና ድርጅት ተቋቁሟል። አንዳንድ ጊዜ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ቢሆን አምስት ሚሊዮን፤ ሰባት ሚሊዮን፤ አስር ሚሊዮን ህዝብ ለመራብ ተቃርቧል እያሉ ዓለም አቀፉን ህዝብ ያስጠነቅቁታል። እነሱ ሃላፊነታቸውን ከራሳቸው ወደዓለም አቀፈ ህብረተሰብ አሸጋግሩታል። እና እነዝያ እስከአሁን ድረስ እህል፤ እነዚህም እዚህ ያሉት መንገስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እህል ያስመጣሉ፤ ያከፋፍላሉ፤ ይሰጣሉ። በዚህ ምክንያት በሰፊው የሞት አደጋ የደረሰበት ከ1977ዓ.ም. ወዲህ አልተከሰተም። ግን ችጋር የለም ማለት አይደለም። እስከአሁንም ድረስ አለ። እነዚያ ሲያቆሙት፣እነዚያ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች በመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም እነ አሜሪካ እና እነ አውሮፓ መስጠቱን ሲያቆሙ ችጋሩ በከፋ መልኩ ድሮ እንደነበረው ገበሬው መርገፍ ይጀምራል። አሁን ያለው በኛ በኢትዮጵያ ሳይሆን በውጪ እርዳታ ኃይል ነው።

<u>ችጋርና ወያኔ</u>

ወያኔ ሲጀምር እኛ ይኼንን እርዳታ ብቻ አንፈልግም፣ ገበሬው እንዲሠራ ለማድረግ እሱን ለማነቃቃት፣ የበለጠ ምርታማ እንዲሆን ለማድረግ እርዳታውን በገንዘብም እያደረጋችሁ ለኛ ስጡን፣ ብዙ ዘዴ አለ ብሎ ነበር። ግን መፍትሄ አልተገኘም። የችጋር መፍትሄ የገበሬ ነፃነት ብቻ ነው። ነፃነት እኮ ኃላፊነትን ይወስዳል። ነፃ የሂነ ሰው ሕይወቱ፣ ኑሮው በእጁ ነው። ኃላፊነቱ አንተ ነው ከተባለና፤ ይኼን መዋጮ አምጣ፣ ይኼን ግብር ክፈል እያለ የሚበዘብዝው ከሌለ እሱ ራስን መቻል አያቅተውም። እንደ ሰው ይዘጋጃል። ለክፉ ጊዜ ያለው ነፃነት ኃላፊነትን በእያንዳንዱ ሰው ላይ ያሳድራል። አሁን ኃላፊነቱ መንግሥት የሚለውም አይደለም። ኃላፊነቱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሆኗል።

# ግንቦትን 97 ማስታወሻ የተቃዉሞ ሰልፍ በአለም ዙሪያ ቀጥሏል

ዋሽንግተን ዲሲ

ግንቦት 23 2008

የቅንጅት ድጋፍ ሰጪዎቸች ማህበረት በመላዉ አለም የግንበቦተት 97 የምርጫን፡ ምክንያት የተደረገዉን፡የሰባዊ፡ረገጣንና የህይወት፡መጥፋትን ማሰታወሻ ከግነንቦት 15 ጀምሮ የሰለላመማዊዉ ተቃወዉሞ፤ የተለያዩ የጸሎትነና ወገን ማሰተማር ቀጥሏል::

በግንቦተት 15 በሜኒሶታ፣ በዋሽንግተን፤ በኒዎዮርክና በኖርዌ የተከሄዱ ሲሆን በግነንቦት 16 ደግሞ ቫንኩቨር ካናዳና በጀኔቫ ስዊዘርላንድ ተካሂደዋል፤



ደቡብ

እትም ከመግባታችን በፊት የደረሰን ዜና በተለያዩ በሰሜን አሚካ፤ ባዉሮፓ፤ ባፈሪካና ባዉስተራልያ ከተሞች ልዩ ልዩ ዝግቶች፡እንዳሉና በቶሮኖቶ በቦስተን፤ በላስ ቬገጋስ፤ በችካጎ፤ በሚኒያፖለልሰና በኦክላንድ ቀኖች የተወሰስኑ መሆናቸሀዉን ተገልጸልናል። በያካባቢዉ፡ስለሚደረጉ፡ዘግጅቶች፡ስለቦታዉ’ ስለቀኑና ስለሰአቱ የቻፐተሮቸን ሀለላፊቸ ወይንም ቅንጅትረ ሰሜን አሜሪካን፡በ kinijitna@kinijitna.org ይጻፌ በ www.Kinijitna.org ይመልከቱ።



ጄኔቫ



ኖርዌ



ሲዊድን

## መብት የተሳትፎ ...

ከገጽ 1 የዞረ

የገደለሽ በላ” እንዷሉ አንድ አጥፊ በዚህ አስነዋሪ ስራው በጥቅም ሲሸለም ሌላ አጥፊ ይጋብዛልና ዛሬም ቢሆን ከገዥዎቻችን ጋር ተመሳጥረው ለአንድነት፡ ለዴሞክራሲና ለፍትህ የቆሙትን ወገኖች እያስጠቁ ያሉት አነዚሁ “…የገደለሽ በላ” አይነቶቹ ናቸው። እነዚህ እንኳን ምርጫቸውን አስተካክለዋል፡ ‘በልተን እንሙት ብለዋል’። እኔን ግራ የገባኝ ይሉኝታ አይሉት ፍርሃት እንዲህ ሃገር ሲታመስ፡ የአንድነት ታሪክ ሲቀለበስ ለትግሉ አስተዋጽዎ ማድረግ ሲገባቸው እጃቸውን አጣጥፈው የተቀመጡት ወገኖች ጉዳይ ነው።

ይሉኝታ አብሮ የመኖር ባህላችን የወለደው አንዱ ክስተት ነው።ይሉኝታ እንደ አግባቡ ጠቃሚም ጎጂም ሊሆን ይችላል። የእናቶቻችንና የአባቶቻችን ይሉኝታ ወግ ነበረው። እንዴት ብትሉኝ ፤በወገንና በሃገር ጉዳይ ላይ ይሉኝታ አያውቁም ነበር። ይልቅስ ዴሞክራሲንና ፍትህን በጠየቀ ወገን ሲጠቃ እጅን አጣምሮ መመልከቱ ይመስለኛል “ሰው ምን ይለኛል” ሊያሰኝ የሚገባው ። የትግሉን ጎራ ከሩቅ የሚመለከቱት ወገኖች ስለ ኢትዮጵያዊነት ሲጨነቁ ስለ ወገኖቻቸው ያላቸውን ምኞት ሲደረድሩ ስለ ሃይማኖታቸውና ስለ ባህላቸው ያላቸውን ቀናኢነት ሳስተውል በጣም እኮራለሁ፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ወገኖች የሚጨነቁለትን እኛነታችንን ከጥፋት ለማዳንና ለትውልድ ለማቆየት በሚደረግ ትግል ውስጥ ሳጣቸው ግራ ይገባኛል።ተግባራዊ ተሳትፎ ሳያደርጉ ለውጥ መጠበቅ ያልዘሩትን እንደማጨድ ይመስለኛል።

የህልውናችን እና የዕድገታችን መሰረት በተፈጥሮ የተሰጠን የሰብዓዊ መብት ጸጋ ነው ብዬ አምናለሁ። የሰው ልጅ ሰብዓዊ መብቱ ባልተረጋገጠበት ህብረተሰብ ውስጥ ዘላቂ ሰላምና ዕድገት ይመጣል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው። ለዚህ ነው ዛሬ የማህበራዊ ሳይንስ ጠበብቶች ማህበራዊ ዕድገትን ከሰባዊ መብት መከበር ጋር በቀጥታ የሚያይዙት። እንግዲህ አስተውሉት፤ በኋላ ቀርነት በርሃብና በዕርዛት የምንታወቀው የዚህች ሃገር ልጆች ለእድገታችንና ለህልውናችን መሰረት ከሆነው ለዴሞክራሲና ለሰባዊ መብት መከበር ከሚደረግ ትግል ርቀን ተመልካች ስንሆን አይገርምም?
ብዙዎቹ የሩቅ ተመልካቾች በገዢዎቻችን የፕሮፖጋንዳ ስራ ግራ የተጋቡ ይመስለኛል። እነ መለስ ዜናዊ ከትናንት ዛሬ አንጀታቸው ራርቶ ኢትዮጵያዊነታቸው አገርሽቶ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብታችንን ያከብሩልን ይሆናል ብለው የሚጠብቁ ቢኖሩ አይደንቀኝም፤ ምክንያቱም ስልጣን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ እንደዚሁ በተስፋ እንጀራ ሲደልሉን ነው።

KINIJIT NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (KNAASO)
766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org

# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የአለም አቀፍ የቅንጅት/አንድነት ድጋፍ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ተመሰረተ!

ግንቦት 10 2000 ዓ.ም

በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓት እንዳይገነባና የአገራችን አንድነት ተጥብቆ እንዳይቆይ፣ የተደነቀሩ በርካታ መሰናክሎች አሉ። በኛ እምነት እነዚህ መሰናክሎች አምባገነን አገዛዞች የፈጠሩት ብቻ ሳይሆኑ በተጓዳኝ ከእኛዉ ድክመቶች የተነሳ የተፈጠሩም ናቸዉ።

ከነዚህም መሰናክሎች አንዱ በጋራ የመስራት ባህል በእኛ ዘንድ አለመኖሩ ነዉ። አቅማችንን፣ ገንዘባችንና እዉቀታችንን በተቀላጠፈ መልኩ በጋራ አለመጠቀማችን አንዱ ችግራችን ነበር።

በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ የሚደረገዉን ሰላማዊና ትግል ለማገዝ፣ እንዲሁም በዉጭ አገር የሚኖረዉን ወገናችን በአገሩ ጉዳይ ላይ የጠራ መረጃ አግኝቶ በትግሉ ላይ እምነትና ጽናት እንዲኖር ለማድረግ፣ የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ማህበርና የቅንጅት ካናዳ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ምክር ቤት የአለም አቀፍ የቅንጅት/አንድነት ድጋፍ ድርጅቶችን የጋራ መድረክ መስርተናል። በዚህ መድረክም በመጠቀምና በአንድነት አቅማችንና ጉልበታችንን በማስተባባር የኢትዮጵያ ሕዝብ የመብቱና የአገሩ ባለቤት እንዲሆን የምናድርገዉን ድጋፍ ከመቼዉም በበለጠ እናጠናክራለን።

በኢትዮጵያ ያለዉ ፓለቲካ አስቸጋሪና ፈታኝ፣ እንደዚሁም እልህ አስጨራሽ መሆኑ አይካድም። በዚህም ከባድ ሁኔታ ዉስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲ ሥርዓት መገንባት የሚያደርገዉን ትግል፣ ሰላማዊ በሆነና በሰከነ መንገድ ለመምራት፣ እንዲሁም የሚያስከፍለዉን መስዋእትነት ለመክፈል እየተንቀሳቀሱ ላሉት የቀድሞ ቅንጅት የአሁኑ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ አመራር አባላት ያለንን ታላቅ አድናቆትና ፍቅር በዚሁ አጋጣሚ እንገልጻለን።

ከጎናቸዉ እንደሆንንና በቅርቡ የሚጠሩት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ በተሳካ ሁኔታ እንደሚፈጸም ያለንን ተስፋ እየገለጽን ከኛ በኩል የሚጠበቀዉን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁነታችንን በድጋሚ እናረጋግጣለን።

ኢትዮጵያዉያን ከተደራጁና ከተባበሩ መፈንቀል የሚያቅታቸዉ ድንጋይ አይኖርም። መድረስ የሚፈልጉበት ደረጃ መድረስ ይችላሉ። ቁልፉ ትብብር፣ አንድነት፣ የመንፈስ ጽናትና ትእግስት ነዉ ብለን ስናምን በሌሎች አህጉራት (አፍሪካ፣ አዉሮፓና አዉስትራሊያ) ያሉ ድጋፍ ማህበራት ይህንን ፎረም እንዲቀላቀሉ ጥሪ እናቀርባለን።

መብት የተሳትፎ ዉጤት ነዉ !